# የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዴት ይታወቃል?

## በዲ/ን ያረጋል አበጋዝ

### ፩. የእግዚአብሔር ፈቃድ (ፈቃደ እግዚአብሔር) ምንድን ነው?

የእግዚአብሔር ፈቃድ ስንል እግዚአብሔር ወድዶና ፈቅዶ እንዲሆን የሚያደርገውን ነገር እና እንዲሆን የሚፈቅደውን (ከመሆን የማይከለክለውን) ነገር ያመለክታል። የእግዚአብሔር ፈቃድ የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገለጥበት አንዱ መንገድ ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ቸር ነው፣ መሐሪ ነው፣ ደግ ነው፣ ...ፈቃዱም እንዲሁ ነው እርሱ ወድዶና ፈቅዶ በሚያደርገው ነገር ሁሉ እነዚህ የባሕርያቱ መገለጫዎች፡- ቸርነት፣ ደግነት፣ ምሕረት ወዘተ አሉ።

እንዲሁም የእግዚአብሔርን አሠራር የሚመራውና ክሂሉን የሚወስነው ፈቃዱ ነው። እግዚአብሔር የሚያደርገው ነገር ማድረግ የሚችለውን ሁሉ ሳይሆን ፈቃዱ የሆነውን ብቻ (ከባሕርዩ ጋር የሚስማማውን ብቻ) ነው የሚፈጽመው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ዓለምን ማጥፋትና እንዳልተፈጠረ ማድረግ ይችላል። ነገር ግን ማድረግ ስለሚችል ብቻ (ይህን ለማድረግ ክሂል ስላለው ብቻ) አያደርገውም፤ ፈቃዱ ማጥፋት አይደለምና። ስለሆነም ማንኛውንም ጉዳይ እግዚአብሔር ማድረግ ስለሚችል ብቻ ያደርገዋል ማለት ስሕተት ነው። እርሱ የሚያደርገው ከቅድስናውና ከባሕርዩ ጋር ተስማሚ በሆነ መንገድ ነው። ይኽ ደግሞ ፈቃደ እግዚአብሔር የምንለው ነው።

የእግዚአብሔር ፈቃድ እጅግ ትልቅና ረቂቅ ነው። መጽሐፍም እንዲህ ይላል "የጥበቡን ምስጢር ቢገልጥልህ ማስተዋሉ ብዙ ነውና።.. የእግዚአብሔርን ጥልቅ ነገር ልትመረምር ትችላለህን? ወይስ ሁሉን የሚችል አምላክ ፈጽመህ ልትመረምር ትችላለህን? ከሰማይ ይልቅ ከፍ ይላል፤ ምን ልታደርግ ትችላለህ? ከሲኦልም ይልቅ ይጠልቃል፤ ምን ልታውቅ ትችላለህ? ርዝመቱ ከምድር ይልቅ ይረዝማል ከባሕርም ይልቅ ይሰፋል። እርሱ ቢያልፍ፥ ቢዘጋም፥ ጉባኤንም ቢሰበስብ፥ የሚከለክለው ማን ነው" /ኢዮ ፲፩፥፮-፲/

## ፪. የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቀው እንዴት ነው?

እግዚአብሔር ፈቃዱን ለእኛ መግለጥ ፍላጎቱ ነው። ሥነ ፍጥረትን የፈጠረው፣ ቅዱሳት መጻሕፍትን የሰጠው፣ በኋላም የባሕርይ ልጁን በሥጋ የላከው ፈቃዱን በግልጥ እንድናውቅ እንዲሁም በዚያ መሠረት እንድንመራና እንድንኖር ጽኑ ፍላጎቱና ፈቃዱ ስለሆነ ነው። ሐዋርያው "....እንደ አሳቡ ፥ የፈቃዱን ምስጢር አስታውቆናልና" ያለው ለዚህ ነው። /ኤፌ.፩፥፱/

### የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምናውቅባቸው ዋና ዋና መንገዶች

- **መጽሐፍ ቅዱስ**

እግዚአብሔር ፈቃዱ ምን እንደሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት በተለያየ መንገድና ሁኔታ በግልጽ አስተምሮናል። ቅዱሳት መጻሕፍት የተሰጡበት ዋና ዓላማ ከእግዚአብሔር ጋር እንዴት መኖር እንዳለብን? ለመዳን ምን ማድረግ እንዳለብን? እግዚአብሔር የሚወድደውና የሚጠላው ምን እንደሆነ? አጠቃላይ የእግዚአብሔር ፈቃድና ለሰው ልጆች ያለው ዓላማ ምን መሆኑን ለእኛ ለመንገርና ለማሳውቅ ነው። ይኽን በተመለከተ ቅዱሳት መጻሕፍት ብዙ ይናገራሉ።

ነቢዩ ዳዊት "እግዚአብሔር ይነግሮሙ ለሕዝቡ በመጽሐፍ ወለመላእክቲሁኒ እለ ተወልዱ በውስቴታ፤ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፥ በውስጧም ለተወለዱት አለቆቿ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል" ይላል። /መዝ፹፮፥፮/ እንዲሁም "ከትእዛዝህ የተነሣ አስተዋልሁ፣ ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ጠላሁ። ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው" ይላል። /መዝ ፻፲፰፥፻፭/ የእግዚአብሔር ትእዛዝ አእምሯችንንና ልቡናችንን ፈቃዱን ለማወቅ ብሩህ የሚያደርግ ስለ መሆኑ ሲናገር ደግሞ "ትእዛዙ ለእግዚአብሔር ብሩህ ወያበርህ አዕይንተ- የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው ዓይንንም ያበራል" ይላል። /መዝ፲፰፥፰/

ቅዱስ ጳውሎስም ደቀ መዝሙሩን ጢሞቴዎስን "ከሕፃንነትህም ጀምረህ ክርስቶስ ኢየሱስን በማመን፥ መዳን የሚገኝበትን ጥበብ ሊሰጡህ የሚችሉትን ቅዱሳት መጻሕፍትን አውቀሃል፤" በማለት ዋናውና መሠረታዊ የሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ማለትም የእኛ መዳን በቅዱሳት መጻሕፍት አማካይነት የተሰጠና የተገለጠ መሆኑን ተናግሯል።/፪ጢሞ፫፥፲፭/

ስለሆነም የእግዚአብሔር ፈቃዱ ምን እንደ ሆነና እንዳልሆነ በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ የተነገረ ነው "የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዴት አድርጌ ላውቅ እችላለሁ? ከየትስ አገኘዋለሁ? የሚል ጭንቀት ሊኖር አይገባም በቅዱሳት መጻሕፍት በዓዋጅ የተነገረ ነውና። ለዚህ ደግሞ የእግዚአብሔር እስትንፋስ የሆኑትን የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል መብላትና በውስጣቸው ባለው በትምህርታቸው መጥገብ ግድ ይላል። ለነቢዩ ሕዝቅኤል እንዲህ ተብሎ እንደ ተነገረ- "እርሱም፡- የሰው ልጅ ሆይ ያገኘኸውን ብላ፣ ይህን መጽሐፍ ብላ፥ ሄደህም ለእስራኤል ቤት ተናገር አለኝ። አፌንም ከፈትሁ፣መጽሐፉንም አጐረሰኝ። እርሱም፡- የሰው ልጅ ሆይ አፍህ ይብላ በምሰጥህም በዚህ መጽሐፍ ሆድህን ሙላ አለኝ። እኔም በላሁት በአፌም ውስጥ እንደ ማር ጣፈጠ።" /ሕዝ ፫፥፩-፫/

ቅዱሳት መጻሕፍትን ያልተማረ ሰው ፈቃደ እግዚአብሔርን ለማወቅ በእጅጉ ይቸገራል። በአኗኗራችን፣ በአነጋገራችን፣ በምርጫዎቻችን፣ ወዘተ የምናያቸው ምስቅልቅሎችና ከፈቃደ እግዚአብሔር ጋር የማይስማሙ ድርጊቶቻችን አብዛኛዎቹ በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ጠንቅቆ ካለመረዳት የሚመነጩ ናቸው። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማወቅ ቅዱሳት መጻሕፍትን መማርና ለተማርነውም መታዘዝና ታማኝ መሆን ይገባል። በትንሹ ስንታመን፣ ላወቅነው ቃለ እግዚአብሔር አክብሮት ስንሰጥና በሕይወታችን መተግበር ስንጀምር ሌላውንም በቸርነቱ እየገለጠልንና እየረዳን ይሄዳል። ፈቃዱን ለማድረግ የሚጥርን ሰው እግዚአብሔር የበለጠውን የጥበቡን በር እየከፈተለት ይሄዳል። ጌታችንና መድኃታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር እርሱ ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን ወይም እኔ ከራሴ የምናገር ብሆን ያውቃል" ያለው ለዚህ ነው። /ዮሐ7፥07/

## መጽሐፍ ቅዱሳዊውን እውነታ አዲስ በሚገጥሙ የተለያዩ ሁኔታዎች ላይ መተግበር

መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ አቅጣጫ የሚያሳይና ዋና ዋና የሆኑ መሠረታዊ ጉዳዮችን የሚነግረን ነው እንጂ በእያንዳንዱ ዝርዝርና ተራ ጉዳይ ውስጥ ገብቶ እኛ በአእምሯችን እያብሰሰልነው ያለውን ጉዳይ ሁሉ በቀጥታ "እንዲህ አድርግ'' ወይም "አታድርግ" እያለ የሚነግረን አይደለም። መጽሐፍ

ቅዱስ ሀገራት "ሕገ መንግሥት" እንደሚሉት ያለ ነው። የሀገራት ሕገ መንግሥት የዚያን ሀገር ሕዝብ በተመለከተ አጠቃላይ መሠረቱን የሚጥልና ወሰኑንና ዳርቻውን የሚወስን ነው። ስለ እያንዳንዱ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ፍትሐ ብሔራዊ፤ ወንጀል ነክ፣ ወዘተ ጉዳይ ገብቶ አንቀጽ የሚያትት አይደለም። ነገር ግን በዚያ በሕገ መንግሥቱ መሠረትነት የተለያዩ የማስፈጸሚያ ሕጎችና መመሪያዎች ደረጃ በደረጃ በየዓይነቱ ይወጣሉ።

መጽሐፍ ቅዱስንም በዚህ ዓይነት ሁኔታ ልናየው እንችላለን። ስለ መዳናችንና ዘለዓለማዊ ሕይወትን ለማግኘት ምን ማድረግ እንዳለብን በቅዱሳት መጻሕፍት በግልጽ ተነግሮናል። ከዚያ ውጭ ስላሉ ሌሎች ጉዳዮች ግን አጠቃላይ አቅጣጫና መመሪያ በመስጠት ዳሩንና ድንበሩን ያሳየናል እንጂ ዝርዝር ነገር ላይነግረን ይችላል። ለምሳሌም እያንዳንዱ ሰው በምን ዓይነት የሥራ መስክ መሰማራት እንዳለበት፣ ማንን ማግባት እንዳለበት፣ ምን ዓይነት ቤት እንደሚሠራ ወዘተ አይነግረውም። ስለዚህም የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በሚገባ በመማርና በማስተዋል መጽሐፍ ቅዱስ ላይ በግልጥ ያልተነገሩ ወይም በግልጽ ያልተናገረባቸው ጉዳዮች ሲገጥሙን ቃሉን በሚገባ የተረዳን ከሆነ ጥሩ መሠረትና መነሻ እናገኛለን። አጠቃላዩን የቅዱስ መጽሐፍ አቅጣጫና መመሪያ በዚያ በገጠመን ዝርዝር ጉዳይ ላይ በመተግበርና ከቃሉ አንጻር በመመዘን ምን ማድረግ እንደሚኖርብንና እንደማይኖርብን ፍንጭ እናገኛለን።

- **ከሌሎች ሕይወት መማር**

ከእኛ በፊት ኖረው ካለፉትም ሆነ በዘመናችን ካሉት ከሌሎች ወገኖቻችንም ለእኛ ጠቃሚ የሆኑ ብዙ ትምህርቶችን ማግኘት እንችላለን። እነ ማን ምን አድርገው ከእግዚአብሔር ፈቃድ አፈነገጡ? ምንስ ገጠማቸው? የእግዚአብሔርን ፈቃድ ፈጸሙ የተባሉትስ ምን ስላደረጉና እንዴት ስለኖሩ ነው? የሚለውን ካለፉ ወገኖቻችን (ከደጋጎቹና ከጻድቃን ብቻ ሳይሆን ከክፉዎቹና ከዓመጸኞችም) ሰፊ ትምህርት ማግኘት እንችላለን። መጽሐፍ ቅዱስ የደጋጎቹን ብቻ ሳይሆን የከፉዎቹንም ሰዎች ታሪክ ጽፎ አስቀምጦልናል። ከደጋጎቹም መርጦ ጥሩ ጥሩ ነገራቸውን ብቻ ሳይሆን ድቀታቸውንና ስሕተታቸውንም ሳይደብቅ የጻፈልን ሁለቱም አስተማሪ ስለሆነ ነው። የደጋጎቹ እነርሱን እንድንመስል፤ የክፉዎቹ ደግሞ እነርሱን እንዳንከተልና ስሕተታቸውንና ጥፋታቸውን እንዳንደግም

ነው። ታላቁ አባታችን ቅዱስ ጳውሎስ እሥራኤላውያን ከግብጽ ሲወጡና ከዚያም ኋላ በመንገድ ላይ እያሉ ያደረጉትንና የደረሰባቸውን ካስታወሰ በኋላ “ይህም ሁሉ እንደ ምሳሌ ሆነባቸው፥ እኛንም የዘመናት መጨረሻ የደረሰብንን ሊገሥጸን ተጻፈ” ያለው ለዚህ ነው። /፩ቆሮ ፲፥ ፩-፲፩/

ከመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት መካከል ብዙ የታሪክ መጻሕፍት አሉ። (ለአብነትም፣ መጽሐፈ ኢያሱ፣ መጽሐፈ መሳፍንት፣ መጽሐፈ ሩት፣ መጽሐፈ ሳሙኤል ቀዳማዊና ካልዕ፣ መጽሐፈ ነገሥት ቀዳማዊ እና ካልዕ፣ መጽሐፈ ዜና መዋዕል ቀዳማዊ እና ካልዕ ፣የሐዋርያት ሥራ)። የእነዚህ መጻሕፍት ትምህርት አሰጣጥም እንደ ሕጉ መጻሕፍት አድርግ አታድርግ በሚል ዓይነት ሳይሆን ከነገሥታቱ፣ ከነቢያቱ፣ ከሕዝቡ ከክፉውም ከደጉም ታሪክ እንድንማር ማድረግ ነው። ከዚያ ሁሉ ሰፊ የታሪክ ማዕድ ፈቃደ እግዚአብሔር ምን እንደ ሆነና እንዳልሆነ እጅግ ብዙ ትምህርት እናገኛለን።

- **መጸለይና በማንኛውም በምናደርገው ነገር ሁሉ እግዚአብሔር እንዲመራን ለእርሱ አሳልፎ መስጠት**

እግዚአብሔር ፍላጎታችንንና ሁለንተናችንን የሚያውቅ መሆኑ ግልጽ ቢሆንም እኛ ግን በግልጽ ለእርሱ መንገርና ፈቃዱን መጠየቅ ይኖርብናል። በየዕለቱ አዳዲስ ጉዳዮች ሲገጥሙን እርሱ እንዲመራንና የእኛ ፈቃድ ሳይሆን የእርሱ ፈቃድ ብቻ እንዲፈጸም መጠየቅ ይገባናል። እሥራኤላውያን የዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግረው ምድረ ርስት ሊገቡ ሳለ ከተለያዩ አሕዛብ ጋር በጦርነት ላይ ነበሩ። ኢያሱ በኢያሪኮና በጋይ ያደረገውን ሰሙ። በዚህ ጊዜ ገባዖናውያን ከተባሉት ሕዝብ መካከል ተወጣጥተው የተላኩ ሰዎች ወደ ኢያሱ ወልደ ነዌ መጥተው ስላደረጉት ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር እንዲህ ይላል፡-

“የገባዖን ሰዎች ግን ተንኰል አደረጉ፤ ለራሳቸውም ስንቅ ያዙ በአህዮቻቸውም ላይ አሮጌ ዓይበትና ያረጀና የተቀደደ የተጠቀመም የጠጅ አቁማዳ ጫኑ። ያረጀ የተጠቀመም ጫማ በእግራቸው አደረጉ፤ አሮጌም ልብስ ለበሱ ለስንቅም የያዙት እንጀራ ሁሉ የደረቀና የሻገተ ነበረ። ኢያሱም ወደ ሰፈረበት ወደ ጌልገላ ሄደው ለእርሱና ለእስራኤል ለዎች- ከሩቅ አገር መጥተናል፣ አሁንም ከእኛ ጋር ኪዳን አድርጉ አሉ። የእስራኤልም ሰዎች ምናልባት በመካከላችን የምትቀመጡ እንደ ሆነ እንዴትስ ከእናንተ ጋር ቃል ኪዳን እናደርጋለን? አሏቸው። ኢያሱንም እኛ ባሪያዎችህ ነን አሉት።

“ኢያሱም፡ እናንተ እነማን ናችሁ? ከወዴትስ መጣችሁ? አላቸው።... እነርሱም አሉት፡- ከአምላክህ ከእግዚአብሔር ስም የተነሣ እጅግ ከራቀ አገር ባሪያዎችህ መጥተናል። ዝናውንም፥ በግብጽም ያደረገውን ሁሉ፥ በዮርዳኖስ ማዶም በነበሩት በሁለቱ በአሞራውያን ነገሥታት፣ በሐሴቦን ንጉሥ በሴዎን፣ በአስታሮትም በነበረው በባሳን ንጉሥ በዐግ ያደረገውን ሁሉ ሰምተናል። ሽማግሌዎቻችንም በምድራችንም የሚኖሩት ሁሉ፡- ለመንገድ ስንቅ በእጃችሁ ያዙ፥ ልትገናኟቸውም ሂዱ፣ እኛ ባሪያዎቻችሁ ነን፣ አሁንም ከእኛ ጋር ቃል ኪዳን አድርጉ በሏቸው አሉን። ወደ እናንተ ለመምጣት በተነሣንበት ቀን ይህን እንጀራ ትኩሱን ለስንቅ ከቤታችን ወሰድነው፣ አሁንም እነሆ ደርቋል ሻግቷልም። እነዚህም የጠጅ አቁማዳዎች አዲስ ሳሉ ሞላንባቸው፣ እነሆም ተቀድደዋል፤ መንገዳችንም እጅግ ስለ ራቀብን እነዚህ ልብሶቻችንና ጫማዎቻችን አርጅተዋል። ሰዎቹም ከስንቃቸው ወሰዱ፥ እግዚአብሔርንም አልጠየቁም። ኢያሱም ከእነርሱ ጋር ሰላም አደረገ በሕይወት እንዲተዋቸውም ከእነርሱ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ፣ የማኅበሩም አለቆች ማሉላቸው ::” /ኢያ ፱፥ ፫—፳/

ምንም እንኳ ኢያሱ እግዚአብሔር እንደማይለየውና ከእርሱ ጋር እንደሚሆን የነገረው ቢሆንም እነዚህ ሰዎች መጥተው ሲጠይቁት እግዚአብሔርን በጸሎት መጠየቅ ነበረበት:: ነገር ግን ያን ሳያደርግ እንዲሁ የሰዎቹን ቃል በመስማት ብቻ ለገባዖናውያን ማለላቸው:: ከዚያም ነገሩ እነርሱ እንዳሉት ከሩቅ አገር የመጡ ሳይሆን እዚያው እሥራኤላውያን ከሰፈሩበት ቦታ አካባቢ የነበሩ ሰዎች መሆናቸው ታውቀ፤ “ከእነርሱም ጋር ቃል ኪዳን ካደረጉ ከሦስት ቀን በኋላ ጎረቤቶቻቸው እንደ ሆኑ በመካከላቸውም እንደ ኖሩ ሰሙ::” /ኢያ.፱፥ ፲፮/

እግዚአብሔርን ምን ጊዜም በጸሎት መጠየቅ የሚጠቅመው እንደዚህ ዓይነት ስሕተቶች ላይ ላለመውደቅ ነው። ልበ አምላክ ዳዊት “ምህረኒ እግዚኦ ለገቢረ ፈቃድከ እስመ አምላኪየ አንተ ወመንፈስከ ቅዱስ ይምርሐኒ በምድረ ጽድቅ፤ አንተ አምላኬ ነህና ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ፣ ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ በማለት የጸለየው ለዚህ ነው:: /መዝ ፻፵፪ ፥፲/ እንዲሁም ይኸው አባታችን ዳዊት ከፍልስጥኤማውያን ጋር በነበረበት ውጊያ ወደ ጦርነት ከመሄዱ በፊት “ዳዊትም፡- ወደ ፍልስጥኤማውያን ልውጣን? በእጄስ አሳልፈህ ትሰጣቸዋለህን?” ብሎ እግዚአብሔርን ይጠይቅ ነበር :: እግዚአብሔርም ይመልስለት ነበር፡- “እግዚአብሔርም

ዳዊትን፦ ፍልስጥኤማውያንን በእርግጥ በእጅህ አሳልፌ እሰጣቸዋለሁና ውጣ አለው::" /፪ ሳሙ ፭፥፲፱/ ዳዊት በጦርነት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በሁሉም ነገሩ እግዚአብሔርን ሳይጠይቅ አያደርግም ነበር:: “ከዚያም በኋላ ዳዊት፦ ከይሁዳ ከተሞች ወደ አንዷቱ ልውጣን? ብሎ እግዚአብሔርን ጠየቀ እግዚአብሔርም፦ ውጣ አለው:: ዳዊትም ወዴት ልውጣ? አለ እርሱም፦ ወደ ኬብሮን ውጣ አለው ::” /፪ ሳሙ፪፥ ፩/

- **ምክር መጠየቅ**

እግዚአብሔር በሰዎች አማካይነት የሚያስፈልገንን ነገር ሊነግረንና ሊመክረን ይችላል። በእርግጥ የምክር ጉዳይ ከፍተኛ ጥንቃቄ ያስፈልገዋል ጥሩ መካር እንዳለ ሁሉ መጥፎ መካርም አለና። ሰዎች የሚሰጡንን ምክር ከቅዱሳት መጻሕፍት፣ ከአባቶቻችን ሕይወትና ትምህርት ጋር የሚቃረን መሆን አለመሆኑን መመዘን የሁል ጊዜም ተግባራችን መሆን አለበት። ይኽ እንዳለ ሆኖ በውስጣችን ከብዶ፤ መያዣና መጨበጫው ጥፍት ብሎ የሚያስጨንቀንን ነገር ለሰዎች ስናካፍለው፤ እግዚአብሔር ለእኛ ካለው አባታዊ ደግነት የተነሣ በዚያ ሰው አማይነት ውስጣችንን ሊነግረንና የፈቃዱን አቅጣጫ ሊያመለከተን ይችላል።

- **እግዚአብሔርን መውደድ**

ለእግዚአብሔር ያለን ፍቅር እየጨመረ በሄደ መጠን፣ እርሱን አምላካችንን የበለጠ በወደድነው መጠን እርሱ የሚወድደውን የበለጠ እያወቅን እንሄዳለን።

እናት ልጇ የሚፈልገውን ነገር ፍላጎቱን በቃላት መግለጽ ከመቻሉ በፊት ታውቀዋለች። እኛም እንዲሁ ነው። እግዚአብሔርን በወደድነው መጠን እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር የበሰጠ እያወቅን እንመጣለን። በአንጻሩም ደግሞ ለእርሱ ያለን ፍቅር እየደከመ በሄደ መጠን ፈቃዱን ማወቅና

መለየት እየተሳነን ይሄዳል፡፡ ፍቅረ እግዚአብሔር የሕግጋቱ ሁሉ መጀመሪያና መጠቅለያ የሆነው ለዚህ ነው፡፡

- **የመንፈስ ቅዱስን ድምፅ ማዳመጥ**

ምናልባት እያደረግነው ያለው ነገር ወይም ልናደርገው በሒደት ላይ ያለው ጉዳይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆነ ነገር ከሆነ መንፈስ ቅዱስ በውስጣችን ይናገራልና ያን ማዳመጥ ይገባል፡፡ ከውስጣችን በጸጥታ ውስጥ ሲናገረን እንሰማዋለን፡፡ ውስጣችን ዕረፍት እንዲያጣ ምቾት እንዳይሰማን . . . የሚያደርግ ነገር ካለ እንዲህ ዓይነቱ ስሜት ሁል ጊዜም ከእግዚአብሔር ነው ብሎ መደምደም ባይቻልም ምናልባት የመንፈስ ቅዱስ ድምፅም ሊሆን ይችላልና ማዳመጡ መልካም ነው፡፡

- **ሕሊናን ማዳመጥ**

ሐዋርያው "ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛት ግድ ነው" እንዳለ ሕሊናን ማዳመጥም ተገቢ ነው፡፡ /ሮሜ፲፫፥፭/ ሕሊናችን አንድ ነገ የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለመሆኑን የምንለካበት ሚዛን ነው፡፡ ስለዚህ ሕሊናችንን ለፍላጎታችን ሳናስገዛና ለስሜታችን እንዲያደላ ሳናደርግ እንደ እውነተኛ ዳኛ አድርገን በፊታችን ያለውን ጉዳይ ከእግዚአብሔር ፈቃድ አንጻር እንመዝንበት፡፡ ጉዳዩ በሕሊናችን ሚዛን የማይደፋ ሆኖ ከታየን ወይም ደግሞ ሕሊናችን ዕረፍት ካጣ፣ ከተረበሸ … በዚያ ጉዳይ ወይም ድርጊት ላይ ጥያቄ ምልክት አለ ማለት ሊሆን ይችላል፡፡ ሆኖም የራስን ስሜትና ሐሳብ ከፈቃደ እግዚአብሔር ጋር ማደባለቅ አይገባም፡፡

አንድ ሐሳብ ደጋግሞ በሕሊናችን ስለተመላለሰ ብቻ እውነትና የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ሊመስል ስለሚችል ከሥጋ ስሜትና ፍላጎት የመነጨ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ ደግሞ ጊዜ መስጠት ወሳኝ ነው፡፡ ከሥጋና ከደም የሆነ ነገር ጊዜ ሲያልፍ እየጠፋና እየደበዘዘ ሲመጣ ከእግዚአብሔር የሆነ ነገር ደግሞ እየጎላና እየጠነከረ ይሄዳል፡፡

- **እግዚአብሔርን በትዕግሥትና በትሕትና ሆኖ መጠበቅ**

እግዚአብሔር ፈቃዱን ለእኛ የሚገልጥበትን ጊዜና ሁኔታ (መንገድ)እርሱ በሚወድደውና በሚፈቅደው መንገድ እንዲያደርገው ለእርሱ ልንተውለት ይገባል እንጂ እኛ መወሰንና መምረጥ የለብንም። እኛ እንዲህ ቢሆን የምንለው መንገድ መኖሩ ስሕተት ነው ማለት ሳይሆን፤ የግድ በዚያ መንገድ ካልሆነ ማለት ግን ተገቢ አለመሆኑን መዘንጋት አይገባም። እግዚአብሔር ለእኛ የሚገልጥልን ሕሊናችንና ዐቅማችን ያን ለመቀበል ዝግጁ ሲሆን ብቻ ነው። እግዚአብሔርን በሕልም ወይም በራእይ ወይም እንዲህ ባለ ሁኔታ ፈቃድህን ግለጥልኝ ብሎ አስቀድሞ መወሰን አይገባም። በምን ዓይነት መንገድ ቢገልጥልን እንደሚጠቅመን እርሱ ስለሚያውቅ ለእርሱ ልንተውለት ይገባል።

ሕልምና ራእይም አስተማማኝ መንገዶች አይደሉም። ይልቁንም እነዚህ ነገሮች ሰይጣን ብዙዎችን በምትሐት ያሳሳተባቸውና ወደ ጥፋት ጎዳና የመራባቸው ነገሮች ናቸው። አብርሃም አባታችንን ባለጠጋው ለራሱ የለመነው ልመና እንደማይሆንለት ካወቀ በኋላ ገና በሕይወተ ሥጋ ያሉትን ወገኖቹን ያስተምራቸው ዘንድ አልዓዛር ከሞት ተነሥቶ ሄዶ እንዲያስተምራቸው በጠየቀ ጊዜ አብርሃም መልሶ “ሙሴና ነቢያት አሏቸው እነርሱን ይስሙ” አለው። ባለጠጋውም መልሶ “አይደለም፥ አብርሃም አባት ሆይ፥ ነገር ግን ከሙታን አንዱ ቢሄድላቸው ንስሐ ይገባሉ” ባለው ጊዜ፤ አብርሃም እንደ ገና “ሙሴንና ነቢያትንም የማይሰሙ ከሆነ ከሙታንም እንኳ አንድ ቢነሣ አያምኑም” ያለው ለዚህም ነበር። /ሉቃ ፲፮ ፳፯-፴፩/ “ከሞት ተነሥቼ መጣሁ፣ በራእይ ታዘዝሁ፣ ሕልም አለምሁ … ” እያሉ ለሚያሳስቱ ለርኩሳን መናፍስት መሣሪያዎችና ተንኮሎች መግቢያ በር እንዳይከፈትላቸው ለማድረግ ነው። እናደርገው ዘንድ የሚያስፈልገን የእግዚአብሔር ፈቃድ በቅዱሳት መጻሕፍት በጥቁርና በነጭ የተጻፈልን ስለሆነ ሌላ መገለጥና ከሙታን የተነሣ ሰው መምህርነት አያስፈልገንም።

ለነገሮች ጊዜ መስጠት አጅግ አስፈላጊ ነገር ነው። በጊዜ ሒደት ውስጥ የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውንና ያልሆነውን ፍንትው አድርጎ መለየት ይቻላል። አንድ ጉዳይ የሚያስጨንቀን ወይም ፈቃደ እግዚአብሔር መሆን አለመሆኑ ግራ አጋብቶን ሊሆን ይችላል ።በዚህ ሁኔታ ላይ ስንሆን ከስሜታዊነትና ወደፊት በጊዜ የሚገለጠውን ነገር አስቀድመን ማወቅ ካለመቻላችን የተነሣ እንጨነቃለን። እየቆየ ሲሄድ ግን አእምሯችን የተሻለ እየተገነዘበው፣ እውነታው ፍንትው ብሎ

እየተገለጠ ስለሚሄድ ጉዳዩን በአግባቡ መረዳትና መለየት በእጅጉ ቀላል እየሆነልን ይመጣል። እንዲሁም እግዚአብሔር ወዲያውኑ እውነቱን ቢነግረን አእምሯችን ሊቀበለው የሚከብደውን ነገር ቀስበቀስ ሲገልጥልን ለመቀበል የነበረው ክብደት ይቀንሳል። ውስጣችን እየተረዳውና እየተገነዘበው ይሔዳል። በዚህም መጀመሪያውኑ ብናውቀው ሊደርስብን ይችል ከነበረው ድንጋጤና የሕሊና መታወክ ያድነናል። እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ በሒደት የሚገጥሙንን ነገሮች በአንድ ጊዜ የማይገልጥልን አንዱ ምክንያት ይኽ ነው። ስለዚህ እኛ ባልነው ጊዜ ሳይሆን ለእኛ በሚጠቅመን ሁኔታና ጊዜ ፈቃዱን እንዲያስታውቀን እግዚአብሔርን በትዕግሥትና በትሕትና ሆኖ መጠበቅ ተገቢ ነው።

## ፫. በፈቃደ እግዚአብሔር ውስጥ የእግዚአብሔርንና የእኛን ድርሻ እንዴት መለየት እንችላለን?

ይኽን መለየት የሚቻለው እኛ የራሳችንን ድርሻ ከተወጣን በኋላ ነው። በቅዱሳት መጻሕፍትና በቤተ ክርስቲያን ሕይወት በተገለጠው ፈቃዱ መሠረት ሁኔታውና ጊዜው የፈቀደልንን ያህል እስከ መጨረሻው ድረስ ዓቅማችንን አሟጠን ከተጠቀምንና ማድረግ ያለብንን ካደረግን በኋላ ያ ነገር ካልሆነ የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም ማለት ይቻል ይሆናል። አለዚያ ግን በእኛ ስንፍና ወይም ስሕተት ምክንያት የሚመጣውን ነገር ሁሉ “የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው” ወይም “የእግዚአብሔር ፈቃድ ስላልሆነ ነው” ማለት አግባብ አይደለም። የእኛን ስሕተትና ስንፍና ሁሉ እንዲሁ በእግዚአብሔር ላይ ማሳበብም ከታላላቅ ስሕተቶችና ኃጢአቶች ወገን ስለሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ልበ አምላክ የተባለ ዳዊት የእግዚአብሔርን ቤተ መቅደስ ለመሥራት አጥብቆ ተመኘ። በጸሎትም፣ በቁሳዊ ዝግጅትም የሚቻለውን ሁሉ አደረገ። በመጨረሻ ግን ቤተ መቅደሱን የሚሠራው እርሱ ሳይሆን ልጁ ሰሎሞን እንደ ሆነ ተነገረው። በነቢዩ በናታን አማካይነት ፈቃደ እግዚአብሔር ከነምክንያቱ

እንዲህ ተብሎ ተነገረው - “… የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ወደ እኔ መጣ እጅግ ደም አፍስሰሃል ታላቅም ሰልፍ አድርገሃል፣ በፊቴ በምድር ላይ ብዙ ደም አፍስሰሃልና ለስሜ ቤት አትሠራም።" /፩ዜና.፳፪ ፥ ፰/ ዳዊት ማድረግ የነበረበትን እንዲያ ባያደርግ ኖሮ ቤተ መቅደሱን መሥራት አለመሥራቱ የእርሱ ጉድለት ውጤት ይሁን ወይም የእግዚአብሔር ፈቃድ አለመሆኑ በግልጽ አይታወቅም ነበር። እግዚአብሔርም ቤተ መቅደሱን በተመለከተ ፈቃዱን በግልጽ የነገረው ዳዊት የራሱን ድርሻ፣ በጸሎትም፤ ለሥራው በሚያስፈልገው ቁሳዊ ዝግጅትም ፤ ሁሉንም በአግባቡ ስለተወጣ ነበር።

የእግዚአብሔርን ሥራ ለማየት፣ ፈቃዱን ለመረዳት ሁል ጊዜም ቢሆን ሰው የራሱን ድርሻ ማወቅና መወጣት አለበት። በቃና ዘገሊላ አገልጋዮቹ ጋኖቹን ውኃ ሞሉ። ጌታችንና መድኃኒታችን ደግሞ እነርሱ ቀድተው በጋኑ ውስጥ የሞሉትን ውኃ ወደ ወይን ጠጅነት ለወጠው። የሁላችን ጌታና መድኃኒታችን ደቀ መዛሙርቱን መረባቸውን ወደ ባሕሩ እንዲጥሉ ሲያዛቸው እንደ ታዘዙት አደረጉ። እርሱ ደግሞ መረቦቻቸውን በዓሣዎች ሞላቸው። / ዮሐ.፳፩፥፲፪/ ጌዴዎን ከምድያማውያን ጋር ለመዋጋት የራሱን ዝግጅት አድርጎ ሲዘምት “ኃይል ዘእግዚአብሔር ኩናት ዘጌዴዎን - ኃይልን ሰጥቶ ድል ማድረግ የእግዚአብሔር ነው፣ ሠይፍ ታጥቆ መዝመት ደግሞ የጌዴዎን ድርሻ ነው” አለ። /መሣ ፯፥፳/ እንዳለውም ብዙ ዘመን ባስጨነቋቸው በምድያማውያን ላይ እግዚአብሔር ድልን ሰጣቸው። የራሳችንን ድርሻ ባለመወጣታችን ምክንያት ሳይሆን የሚቀረውን ነገር ሁሉ “አይ፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ባይሆን ነው" እያሉ በእግዚአብሔር ላይ ማሳበብ ድርብ በደል ነውና ማስተዋልና መጠንቀቅ ያስፈልጋል።

ታላቁ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ወገኖቹን ከግብጻውያን ጭቆናና መከራ ነጻ ለማውጣት ምኞቱና ጉጉቱ ከልጅነቱ ጀምሮ በውስጡ ይመላለስ ነበር። ሆኖም ግን አርባ ዓመት ሲሆነው ወገኖቹን ሊጎበኝ በወጣ ጊዜ በግብጻዊው ሲገፉና ሲበደል ላየው ለዕብራዊው በማበር ያደረገው ድርጊት ግን የተሳሳተ አካሄድ ነበር። ይህም የእግዚአብሔርን ፈቃድና አሠራር እንዲማርና ለዚያም ዝግጁ እስኪሆን ድረስ ለአርባ ዓመታት ያህል ወደ ምድያም በረሐ በስደት እንዲሄድ አደረገው። ጊዜው

ሲደርስ እግዚአብሔር ሕዝቡን በምን ዓይነት ሁኔታ እንደሚያወጣቸው ገለጠለት፤ የሙሴ ምኞትም ተፈጸመ። ከውስጣችን ጥልቅ ፍላጎትና ውሳኔ ሳይኖር የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማየትና መለየት አንችልም። ይኸ ካለ ግን ምናልባት እንደ ሙሴ ከአካሄዳችን የተሳሳተውንና መስተካከል ያለበትን ያርመዋል እንጂ ፈቃዱን ከማድረግ አይከለክለንም፤ ወይም ደግሞ እንደ ዳዊት በግልጥ ያስታውቀናል እንጂ እንዲሁ በብዥታ ውስጥ ወዲያና ወዲህ እየዋዠቅን እንድንኖር አይተወንም።

## ፩. በሕይወታችን የሚገጥመንን ማንኛውንም ነገር፤ መልካምም ሆነ ክፉ፤ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ማለት እንችላለን ወይ?

መልሱ በአጭሩ አንችልም ነው። የእግዚአብሔር ፈቃድ ስንል ሁለት ዓይነት ነው። አንደኛው ቀዳማዊ ፈቃዱ (Antecedent Will) ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ተግባራዊ ፈቃዱ (Subsequent Will) የሚባለው ነው። ይኸ ማለት በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ የሚቀድምና የሚከተል ነገር አለ ማለት አይደለም። በእኛ እሳቤ ቅደም ተከተል የተለያዩ ነገሮች መሆንን ያመለክታልና። የእግዚአብሔር ፈቃድ አንድ ነው። ቀዳማዊና ተግባራዊ (ተከታይ) ፈቃድ መባሉ በመለኮታዊ ፈቃደ እግዚአብሔር ዘንድ መቅደምና መከታተልን የሚያመለክት ሳይሆን (ዘለዓለማዊ ለሆነው አምላክ ይኸ ተገቢ አይደለምና) ፈቃዱ የሚመለከታቸውን ሥነ ፍጥረታት የሚመለከት ነው። ስለዚህ ቀዳማዊና ተግባራዊ ፈቃዱ ሲባል ረቂቁን ፈቃደ እግዚአብሔርን ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው። ቀዳማዊ ፈቃዱ (Antecedent Will) የሚባለው ከእርሱ ከራሱ የሚገኘውና የሚሆነውን ሲሆን ተግባራዊ ፈቃዱ (Subsequent Will) የሚባለው ደግሞ ከእኛ የተነሣ የሚሆነውን ነው።

ፍጥረቱን እግዚአሔር ሲፈጥረው ያዘጋጀለት ነገር በእርሱ በቅድምና የታሰበ (የተዘጋጀ፣ የተፈቀደ) ነው ተብሎ ሊታሰብ ይችላል። ነገር ግን ያ ፍጥረት በራሱ ውድቀት ምክንያት ከዚያ እግዚአብሔር ካዘጋጀለት ፍጻሜና ግብ ሳይደርስ ከቀረ ይህ የመጀመሪያው እግዚአብሔር ለዚያ ፍጥረት ያዘጋጀለት ፍጻሜ ባይሆንም ከመሆን ግን በግድ አያስቀረውም። ተግባራዊ ፈቃዱ የሚባለው ይኸኛው ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር ሰውን ሁሉ የፈጠረው በደስታና በመልካም ሁኔታ እንዲኖር ነው። እንዲሁም ከወደቀ በኋላም ስው በሥጋዌው የሚድንበትን መንገድ ሁሉ አዘጋጅቶለታል። ይኸ ቀዳማዊ ፈቃደ እግዚአብሔር ነው። ነገር ግን አንዳንዶች ወደ ዘለዓለማዊ ሕይወትና ወደ ድኅነት ከሚወስዳቸው መንገድና ድርጊት በተቃራኒ ስለሚጓዙና ስለሚያደርጉ እንዲያ በማድረጋቸው ምክንያት

ምርጫቸው ከሚያስከትለው ነገር አይከለክላቸውም። ይኸም ሆኖ የእግዚአብሔር ፈቃድ ከመፈጸም አይስተጓጎልም። ምክንያቱም እንዲህ ያሉትም በራሳቸው ፈቃድና ምርጫ እንደማይድኑ መለኮታዊ እውቀቱ ጥንቱንም ያውቀዋልና ያ እውቀቱ ነው የሚፈጸመው። እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ከጥንቱ (ከጊዜ እሳቤ ውጭ በሆነ ዘለዓለማዊነቱ) ያውቀዋል። ነጻ ፈቃድ ያላቸውን ፍጥረታት ምርጫና ውሳኔ ግን አስቀድሞ አይወስንም።

እግዚአብሔር ከሰውና ከመላእክት ውጭ ባሉት ፍጥረታት ላይ ፈቃዱ ያለ አንዳች ማወላወል ሙሉ በሙሉ ይፈጸማል። መላእክትንና ሰውን በተመለከተ ግን ነጻ ፈቃድ ስላላቸው እነዚህ ፍጥረታት ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተቃራኒ የሆነ ነገር የማድረግ ነጻነት አላቸው። ተፈትነው ባለፉት በቅዱሳን መላእክት ዘንድም ፈቃዱ ያለ አንዳች መዛነፍ ይፈጸማል። “ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነ እንዲሁም በምድር ይሁን” ብላችሁ ጸልዩ ያለንም ለዚህ ነው። በሰማውያን መላእክት ዘንድ ፈቃዱ ያለ አንዳች መሰናክልና ተቃውሞ ይፈጸማል፣ ይገለጣልና። በዓለመ መላእክት ዘንድ ሳጥናኤል በራሱ ፈቃድ ተነሳሥቶ ባደረገው ዓመጽና ክህደት ከእግዚአብሔር ክብር ተለይቶ፣ ብርሃናዊነቱን አጥቶ፣ ከጸጋና ከቅድስና ተራቁቶ፣ የወደቀ ውዱቅና ጽልመታዊ ሆኗል። ይህ የእግዚአብሔር ፈቃዱ አልነበረም። ማለትም እግዚአብሔር ሳጥናኤልን ሲፈጥረው እንደ ሌሎቹ መላክእት በክብርና በቅድስና እንዲኖር ነበር እንጂ ራሱ መርጦ እንደ ሆነው እንዲሆን አልነበረም። ሆኖም ግን እግዚአብሔር የነጻነት አምላክ ስለሆነ ሳጥናኤል የመረጠውን ዲያብሎስ የመሆን ምርጫ አልከለከለውም።

በሰውም እንዲሁ ነው። ሰውን በአርአያውና በምሳሌው የፈጠረው የክብሩ ወራሾች የቅድስናው ተሳታፊዎች እንድንሆን ነው። ሆኖም ግን ሰዎች እንደየ ፍላጎታቸውና እንደየ ውሳኔያቸው እግዚአብሔርን መተውና ከእርሱ መለየት፣ ሌላ የፈለጉትን መምረጥና መሆን ይችላሉ። እግዚአብሔር እንዲህ ያለው የሰው ውሳኔና ምርጫ እንዲሆን ቀዳማዊ ፈቃዱ አይደለም። ነገር ግን እርሱ ስላልፈለገው ብቻ ሰውን አስገድዶ ወይም አእምሮውን ጠምዝዞ እንዳይሆን አይከለከልውም። እግዚአብሔር ነጻነትን ሲሰጥ ያለ መሸራረፍ ሙሉውን ነውና። ከዚህም የተነሣ መሆናቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ ያልሆኑ፣ ነገር ግን በሰዎች የነጻነት ምርጫ አላግባብ መጠቀም

ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች አሉ፤ ሞልተዋልም። ለአብነትም እግዚአብሔር እንዲሆን የሚያዝዘው ነገር ሌላ፣ የተነገራቸው ሰዎች የሚያደርጉት ነገር ደግሞ ከፈቃደ እግዚአብሔር ተቃራኒ እንደሆነ የሚያሳዩን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሉ። እንደሚከተለው እንመለከተቸዋልን።

- ✓ "ኢየሩሳሌም ኢየሩሳሌም ሆይ ነቢያትን የምትገድል ወደ እርሷ የተላኩትንም የምትወግር፥ ዶሮ ጫጩቶቿን ከክንፎቿ በታች እንደምትሰበስብ ልጆችሽን እሰበስብ ዘንድ ስንት ጊዜ ወደድሁ! አልወደዳችሁምም። እነሆ ቤታችሁ የተፈታ ሆኖ ይቀርላችኋል። እላችኋለሁና፥ በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው እስክትሉ ድረስ ከእንግዲህ ወዲህ አታዩኝም።" /ማቴ ፳፫ ፴፯-፴፱/
- ✓ "ሲቀርብም ከተማይቱን አይቶ አለቀሰላት፥ እንዲህ እያለ። ለሰላምሽ የሚሆነውን በዚህ ቀን አንቺስ ስንኳ ብታውቂ፤ አሁን ግን ከዓይንሽ ተሰውሯል። ወራት ይመጣብሻልና ጠላቶችሽም ቅጥር ይቀጥሩብሻል ይከቡሻልም በየበኩሉም ያስጨንቁሻል፤ አንቺንም በአንቺም ውስጥ የሚኖሩትን ልጆችሽን ወደታች ይጥላሉ፥ በአንቺ ውስጥም ድንጋይ በድንጋይ ላይ አይተዉም፥ የመጎብኘትሽን ዘመን አላወቅሽምና።" /ሉቃ፲፱፥፵፩-፵፬/
- ✓ "በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና:: ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና። በእርሱ በሚያምን አይፈረድበትም፤ በማያምን ግን በአንዱ በእግዚአብሔር ልጅ ስም ስላላመነ አሁን ተፈርዶበታል።ብርሃንም ወደ ዓለም ስለ መጣ ሰዎችም ሥራቸው ክፉ ነበርና ከብርሃን ይልቅ ጨለማን ስለ ወደዱ ፍርዱ ይህ ነው።" /ዮሐ፫፥፲፮-፲፱/
- ✓ "እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።" /ዮሐ ፭፥ ፴፱-፵/
- ✓ "ኑና እንዋቀስ ይላል እግዚአብሔር፣ ኃጢአታችሁ እንደ አለላ ብትሆን እንደ አመዳይ ትነጻለች እንደ ደምም ብትቀላ እንደ ባዘቶ ትጠራለች። እሺ ብትሉ ለእኔም ብትታዘዙ፥ የምድርን በረከት ትበላላችሁ፣ እምቢ ብትሉ ብታምፁም፥ ሰይፍ ይበላችኋል፣ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሯልና።" /ኢሳ.፩ ፲፰-፳/

- ✓ “አንተም፥ የሰው ልጅ ሆይ፥ የእስራኤልን ቤት፦ እናንተ በደላችንና ኃጢአታችን በላያችን አሉ እኛም ሰልስለንባቸዋል፣ እንዴትስ በሕይወት እንኖራለን? ብላችሁ ተናግራችኋል በላቸው :: እኔ ሕያው ነኝና ኃጢአተኛው ከመንገዱ ተመልሶ በሕይወት ይኖር ዘንድ እንጂ ኃጢአተኛው ይሞት ዘንድ አልፈቅድም፥ ይላል ጌታ እግዚአብሔር:: የእስራኤል ቤት ሆይ ተመለሱ ከክፉ መንገዳችሁ ተመለሱ ስለ ምንስ ትሞታላችሁ? በላቸው::” /ሕዝ ፴፫፥፲-፲፩/

እንግዲህ እነዚህ ሁሉ አምላካዊ መልእክታት በግልጽ የሚናገሩት በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰዎችን ማዳን መሆኑን ከዚህም የተነሣ ከጥንት ጀምሮ የምሕረት እጁን ዘርግቶ ወደ እርሱ እንድንቀርብ በተለያየ ሁኔታ የሚጠራንና የሚያስተምረን መሆኑን፤ በሌላ በኩል ደግሞ የእግዚአብሔርን ጥሪ ሰምተው ለመዳን ወደ እርሱ የሚቀርቡ ጥቂቶች የመኖራቸውን ያህል ብዙዎቹ ደግሞ ጥሪውን ቸላ ብለው በራሳቸው መንገድ እየሄዱ የሚጎዱና የሚጠፉ መሆናቸውን ነው:: እግዚአብሔር ማንኛውንም ሰው ይጠራዋል ይመክረዋል እንጂ በኃይል አስገድዶና ነጻነቱን ገፍፎ ያለ ፈቃዱ የእርሱን (የእግዚአብሔርን) ፈቃድ እንዲፈጽም አያደርገውም፤ ይኸ ነጻ ከሆነው ከአምላካዊ ባሕርዩ ጋር የሚስማማ አይደለምና::

በመሆኑም የእግዚአብሔር ፈቃድ የሆነውን በጎውን ነገር እምቢ ብለን በራሳችን ስሜትና ፈቃድ እየተጓዝን የሚደርስብንን ነገር ሁሉ “የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው” ማለት በእግዚአብሔር ላይ መዘበት ነው። ለምሳሌ እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ከግብጽ ምድር ያወጣቸው በቀጥታ ወደ ምድረ ርስት ሊያስገባቸው ነበር። ሆኖም እነርሱ ግን የ0ሥሩን ሰላዮች ቃል ሰምተው በእግዚአብሔር ላይ ስላመጹና የማይገባ ነገር ስለ ተናገሩ የአርባውን ቀን መንገድ የአርባ ዓመት አደረገባቸው፤ በቀጥታው መንገድ ሳይሆን አስቸጋሪና የሚያቃጥል በሆነው በቃዴስ በረሓ በኩል እንዲዞሩና እንዲንከራተቱ አደረጋቸው። የራሳቸው ኃጢአት አርባ ዓመት በምድረ በዳ በሚያቃጥል አሸዋ፣ በውሃ ጥም፣ በእባብና በጊንጥ፣ … እንዲሰቃዩ አደረጋቸው። ከዚያም ከግብጽ ከወጡት ሕዝብ መካከል ከሁለቱ ከኢያሱና ከካሌብ፤ በስተቀር ሙሴና አሮንም ጭምር አንዳቸውም ምድረ ርስትን ሳያዩ በበረሓ ወድቀው እንዲቀሩ አደረጋቸው። ይኽን ሁሉ ያደረገው የእግዚአብሔር ፈቃድ ሳይሆን የራሳቸው ጠማማ ልብና አካሄድ ነበር።

ያን ጊዜ የነበሩት እሥራኤላውያን ብቻ ሳይሆኑ በየዘመኑ የነበሩና የሚኖሩ የሰው ልጆች ብዙዎቹ ፈቃደ እግዚአብሔርን በተለያየ መንገድ ተቃውመዋል። እግዚአብሔር ባዘጋጀው የዕረፍት ውኃና የለምለም መስክ ሳይሆን መከራና ቃጠሎ በበዛበት ሕይወት የዳከሩና የኳተኑ ብዙዎች ነበሩ፣ ዛሬም አለን። ሰው ፈቃደ እግዚአብሔርን በተለያየ ሁኔታ ይቃወማል። አንዳንዱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ በግልጽ በይፋ ይቃወማል። ቅዱስ እስጢፋኖስ አይሁድን "እናንተ አንገተ ደንዳኖች ልባችሁና ጆሯችሁም ያልተገረዘ ፥እናንተ ሁል ጊዜ መንፈስ ቅዱስን ትቃወማላችሁ፤ አባቶቻችሁ እንደ ተቃወሙት እናንተ ደግሞ" በማለት እንደ ተናገራቸው። /የሐዋ፯፥፶፩/ ሌላው ደግሞ በግልጽ ባይቃወምም እንደ ፈቃዱ የሆነ ምንም ነገር ባለማድረግ፣ ፈቃዱን ባለመፈጸም ይቃወማል። "የሰሙትም ሕዝብ ሁሉ ቀራጮች እንኳ ሳይቀሩ በዮሐንስ ጥምቀት ተጠምቀው እግዚአብሔርን አጸደቁ፤ ፈሪሳውያንና ሕግ አዋቂዎች ግን በእርሱ ስለ አልተጠመቁ የእግዚአብሔርን ምክር ከራሳቸው ጣሉ" እንደ ተባለ። /ሉቃ ፯፥፴/

ሌላው ደግሞ ባለማወቅ የሚደረግ ተቃውሞ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ፈቃደ እግዚአብሔርን በጽኑ እየተቃወመ ቤተክርስቲያንን ያሳድድበት የነበረውን የቀደመ ሕይወቱን በሐዘን በማስታወስ "አስቀድሞ ተሳዳቢና አሳዳጅ አንገላችም ምንም ብሆን ይህን አደረገልኝ፤ ነገር ግን ሳላውቅ ባለማመን ስላደረ ግሁት ምሕረትን አገኘሁ" እንዳለ። /፩ጢሞ.፩፥ ፲፫/ በእነዚህ ብቻ ሳይሆን ሰው ፈቃደ እግዚአብሔርን የራሱን መንገድና ፈቃድ በመከተልም ይቃወማል። አይሁድን ከእግዚአብሔር የለያቸውና በኢየሱስ ክርስቶስ ከተገኘው ጸጋ ሁሉ ያራቃቸው እግዚአብሔር በአምላካዊ ፈቃዱ ባጋጀውና በሰጠው መንገድ ሳይሆን ራሳቸው የጽድቅ መንገድ ብለው ባዘጋጁት በመሄዳቸው ነበር። "ወንድሞች ሆይ የልቤ በጎ ፈቃድና ስለ እስራኤል ወደ እግዚአብሔር ልመናዬ እንዲድኑ ነው። በዕውቀት አይቅኑ እንጂ ለእግዚአብሔር እንዲቀኑ እመሰክርላቸዋለሁና። የእግዚእብሔርን ጽድቅ ሳያውቁ የራሳቸውንም ጽድቅ ሊያቆሙ ሲፈልጉ ለእግዚአብሔር ጽድቅ አልተገዙም" ተብሎ እንደ ተነገረ። /ሮሜ.፲፥፩-፫/

**፭ በፈቃደ እግዚአብሔር ዙሪያ ሊስተዋሉ የሚገባቸው አንዳንድ መሠረታዊ ነጥቦች**

ዋናውና መሠረታዊው የእግዚአብሔር ፈቃድ የሰው ሁሉ መዳንና ዘለዓለማዊ የሆነውን ሕይወት ማግኘት ነው። “ሰዎች ሁሉ ሊድኑና እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው እንደ ተባለ” /፩ጢሞ፪፥፫-፬/ እንዲሁም የእግዚአብሔር ፈቃድ ወደ እርሱ በንጽሕናና በቅድስና መቅረባችንና መቀደሳችን ነው። “ይህ የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም መቀደሳችሁ ነውና" እንደተባለ። /፩ተሰ ፬፥፫/ እግዚአብሔር ሌላውን ማንኛውንም ነገር የሚሰጠን ልመናችንን የሚፈጽምልን ከዚህ ከዋናው ፈቃዱ፤ ዘለዓለማዊ ሕይወትን ከማግኘታችንና ከመቀደሳችን፤ ጋር አስካልተቃረነ ድረስ ብቻ ነው። የሚሰጠን ወይም የሚያደርግልን ነገር በመዳናችን ላይ መሰናክል የሚያመጣብንና ፈተና የሚሆንብን ከሆነ አባት እንደ መሆኑ መጠን አስቀድሞ ያስቀርልናል። አባት ለልጁ የማይጠቅመውን ያደርግ ዘንድ አባታዊ ፍቅሩ አያሰናብተውምና።

የእግዚአብሔርን ፈቃድ አግባብነትና ትክክለኛነት፣ እንዲሁም አንድ ነገር የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆን አለመሆኑን የምንመዝነውና የምንለካው በራሳችን ስሜት፣ ፍላጎትና እውቀት መመዘኛነት መሆን የለበትም። እኛ የእግዚአብሔርን አሠራር ለመመዘንና በዚያ ላይ ብይን ለመስጠት ይቅርና የሰዎችን ሥራ እንኳ በአግባቡ ለመረዳትና ለመመዘን ሙሉ በሙሉ እንችላለን ብለን አፋችንን ሞልተን ለመናገር በእጅጉ የሚከብደን ደካሞች ነን። ስለዚህ አንድን ነገር እግዚአብሔር ለምን ዓላማ እንዳደረገውና እንዴት እንዳደረገው ለማወቅ ተፈጥሯዊ ዓቅማችን አይፈቅድልንም። እንዲሁ በድፍረት ተነሥተን “አይ እግዚአብሔር፣ ለምን እንዲህ ያደርጋል? ወይም ለምን እንዲህ አያደርግም" ብለን ሕያው ባሕርይና ማእምረ ኅቡአት በሆነው በእግዚአብሔር ላይ አንደበታችንን እንከፍት ዘንድ መብቱም ዓቅሙም የለንም።

በእኛ ዘንድ ክፉ ተብለው የሚታወቁ ነገሮችን እርሱ ግን የራሱን ዓላማ ለማስፈጸም፣ ቅጣት የሚገባቸውን ለመቅጣት በፈተና ተፈትነው እንደ ወርቅ ነጥረው የሚወጡትን ደግሞ ተዋግተው ድል አድርገው በክብር ደምቀው እንዲወጡና ማንነታቸው እንዲገለጥ ለማድረግ ሊጠቀምበት ይችላል። ቅዱስ እግዚአብሔር በነቢዩ ኢሳይያስ “ብርሃንን ሠራሁ ጨለማውንም ፈጠርሁ ደኅንነትን እሠራለሁ፥ ክፋትንም እፈጥራለሁ፣ እነዚህን ሁሉ ያደረግሁ እግዚአብሔር እኔ ነኝ" የሚለው አገላለጽ

ይህን ያመለክታል። /ኢሳ. ፵፫ ፥፯/ ይኸም ማለት እግዚአብሔር ክፋትን የሚፈጥር አምላክ ሆኖ ሳይሆን በኃጢአታቸው ምክንያት የሚያመጣባቸውን አባታዊ ተግሣጽ እነርሱ እንደ ክፉ ነገር አድርገው ይመለክቱት ስለ ነበር በዚያ በእነርሱ አረዳድ መንገድ ለመግለጽ ነው። ስለሆነም ድርጊቱ ለእኛ ስለ ጎረበጠን ወይም እኛ እንዳሰብነውና እንደምንፈልገው ስላልሆነ ብቻ፣ በዚያውም ላይ እንደ ፈቃዱ ሳንሄድ የሚደርስብንንና በዓለሙ ላይ የሚሆነውን ነገር በማየት ካለማወቅና ካለማስተዋል የመነጨ አስተያየትና ትንታኔ መስጠት አግባብ አይደለም፤ ከባድ ድፍረትና ጽርፈትም ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ከክፋታቸው የተነሣ የሚደርጓቸውን ነገሮች ከአምላካዊ ድንቅና ረቂቅ ጥበቡ የተነሣ የራሱን ሥራ ለመሥራትና ሐሳቡን ዳር ለማድረስ ሊጠቀምባቸው ይችላል። ሆኖም እንዲያ ሲያደርግ እርሱ ከክፉዎቹ ከክፋታቸው አይሳተፍም። ክፋትን እንዲያደርጉም ምክንያታቸው እርሱ አይደለም። ክፉውን የሚያደርጉት(ያደረጉት) ሰዎችም በዚህ ምክንያት ከክፉ አድራጊነትና ከተጠያቂነት ነጻ ሊሆኑ አይችሉም።

ይኸን ሐሳብ በምሳሌ ማየቱ የበለጠ ይረዳ ይሆናል። እሥራኤል የተባለ ያዕቆብ ብኩርናን ማግኘቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። ምክንያቱም ዔሣው ምድራዊና ቁሳዊ ሀብትንና ተድላ ደስታን እንጂ መንፈሳዊ በረከትን የሚሻ ሰው አልነበረምና በረከቱ ይኸን ሲሻ ለነበረው ለያዕቆብ መሆኑ ፈቃደ እግዚአብሔር ነበር። ሆኖም ግን ያዕቆብ በረከትን የወሰደበት የማታለል መንገድ ግን እግዚአብሔር ዘንድ የተወደደ አይደለም። እግዚአብሔር ምን ጊዜም ሐስትንና ተንኮልን ይጸየፋልና። ሆኖም በእናቱ በርብቃ ምክርና በያዕቆብ ፈጻሚነት በተንኮልም ቢሆን በረከቱ ከዔሣው ቀርቶ ለያዕቆብ እንዲሆን ሆነ። እግዚአብሔር ይኸን ዓላማውን በያዕቆብ አካሄድም ቢሆን ፈጽሟል።

ሆኖም ግን ያዕቆብ በረከትን ለማግኘት የሄደበት የማታለል አካሄድ ስሕተት ስለ ነበረ እግዚአብሔር ያዕቆብን በዚያው ባታለለበት መንገድ እንዲታለል አሳልፎ ስጥቶታል። ከዚህም የተነሣ ያዕቆብን የራሱ ልጆች ዮሴፍን ሸጠው ልብሱን ገፍፈው የአውራ ፍየል ደም ነክረው “ይህን አገኘን፣ ይህ የልጅህ ልብስ እንደ ሆነ ወይም እንዳልሆነ እስኪ እየው'' አሉት። እርሱም “የልጄ ቀሚስ ነው፣ ክፉ ውሬ በልቶታል፣ ዮሴፍ በርግጥ ተበጫጭቋል አለ:: ያዕቆብም ልብሱን ቀደደ በወገቡም ማቅ ታጥቆ

ለልጁ ብዙ ቀን አለቀሰ::" /ዘፍ ፴፯÷፴፩-፴፬/ ያዕቆብ ወንድሙን በልብስ እንዳታለለውና እንዳስለቀሰው እርሱን ደግሞ የራሱ ልጆች በዚያው መንገድ አታለሉት፣ አስለቀሱት:: ከዚያም ራሔልን አገባለሁ ብሎ ሰባት ዓመት ከተገዛ በኋላ አባቷ ላባ ሌሊት እኅቷን ልያን በመስጠት አታለለው፤ ራሔልን ለማግኘት ሲል እንደገና ሌላ ሰባት ዓመት ተገዛ። እንዲሁም አጎቱ ላባ ደመወዙን ብዙ ጊዜ እየለዋወጠ ሲያታልለው ኖረ።

የዮሴፍ ወንድሞች ዮሴፍን መሸጣቸው እነርሱ በዚያው ይጠፋል፣ የነገረን ሕልም በእኛ ላይ ከመፈጸም ይቀራል፣ እኛም ይነግሥብናል ከሚል ስጋት ነጻ እንሆናለን ብለው ነበር። ነገር ግን ያ የፈሩትን ነገር ያስቀርልናል ብለው ያደረጉት ድርጊታቸው በተቃራኒው ዮሴፍን በሕልም ያየው ነገር ወደሚፈጸምበት አገርና ሁኔታ እንዲሄድ መንገድ ከፋችና መሰላል ሆነው። ኋላም በረኃብ ምክንያት ግብጽ ሲሄዱ ወንድማቸው ዮሴፍ በግብጽ ላይ ነግሦ አድራጊ ፈጣሪ ሆኖ አገኙት፣ ሰገዱለት። እግዚአብሔር የወንድሞቹን ክፉ ሐሳብና ድርጊት ያዘጋጀውን ሐሳብ ለመፈጸም መጋቢ(አገልጋይ) አድርጎ ተጠቅሞበታል። ሆኖም በእነርሱ ክፋት ውስጥ ፈጽሞ የለም፣ ይኸ ከእርሱ ይራቅ። የዮሴፍ ወንድሞችም ወንድማቸውን የመሸጣቸው ክፋትና ወንጀል በዚህ ምክንያት (ዮሴፍን ወደሚነግሥበትና ሕልሙ ወደሚፈጸምበት ቦታ የመራው በመሆኑ) ከበደል ነጻ ሊሆኑና የእግዚአብሔርን ሥራ እንደ ሠሩ ሊያስቆጥራቸው አይችልም። ቅዱስ እስጢፋኖስ "የአባቶችም አለቆች በዮሴፍ ቀንተው ወደ ግብጽ ሸጡት" በማለት በደለኛነታቸውን የገለጸው ለዚህ ነው።/ የሐዋ፯÷፱/

እነርሱም የሆነ ችግር በገጠማቸው ጊዜ "ወንድማችንን እንጂ እያማጸነን ሳለ ጨክነን ስለ ሸጥነው እኮ ነው ይህ ሁሉ መከራ የሚደርስብን" እያሉ ኃጢአታቸው ሲወቅሳቸውና ሲከሳቸው ኖሯል። እነዚሁ ወንድሞቹ አባታቸው ያዕቆብ ከሞተ በኋላ "ምናልባት ዮሴፍ ይጠላን ይሆናል ባደረግንበትም ክፋት ሁሉ ብድራት ይመልስብን ይሆናል" ብለው በመፍራት ወደ ዮሴፍ መልእክት ላኩ እንዲህም አሉት፡- "አባትህ ገና ሳይሞት እንዲህ ብሎ አዝዟል-- ዮሴፍን እንዲህ በሉት ፡- እባክህን የወንድሞችህን በደል ኃጢአታቸውንም ይቅር በል፥ እነርሱ በአንተ ከፍተውብሃልና አሁንም እባክህ የአባትህ አምላክ ባሪያዎች የበደሉህን ይቅር በል" ከዚያም ቅዱስ መጽሐፍ እንዲህ

ይላል፡-  "ዮሴፍም ይህን ሲሉት አለቀሰ። ወንድሞቹ ደግሞ መጡ በፊቱም ሰግደው እነሆ እኛ ለአንተ ባሪያዎችህ ነን አሉት። ዮሴፍም አላቸው ፡- አትፍሩ እኔ በእግዚአብሔር ፋንታ ነኝን? እናንተ ክፉ ነገርን አሰባችሁብኝ እግዚአብሔር ግን ዛሬ እንደ ሆነው ብዙ ሕዝብ እንዲድን ለማድረግ ለመልካም አሰበው። አሁንም አትፍሩ እኔ እናንተንና ልጆቻችሁን እመግባችኋለሁ:: አጽናናቸውም፣ ደስ እሰኛቸውም።" /ዘፍ ፶፣ ፲፭-፳፩/ እንግዲህ ይኽ ሁሉ የሚያሳየን በደላቸው ውስጣቸውን ሲያስቃያቸው የኖረ መሆኑን ነው። ስለዚህ ኃጢአተኛውም ኃጢአቱን በክፉ ሕሊናውና በራሱ ፈቃድ መሠረት ይፈጽማል ።እግዚአብሔር ደግሞ ከጥበቡ ጥልቀትና አይመረመሬነት የተነሣ የክፉዎችን ክፋት ቅጣት የሚገባቸውን ለመቅጣት፣ እንደ ወርቅ በእሳት ተፈትነው ነጥረው የሚወጡትን ደግሞ እንዲያ እንዲገለጡ ለማድረግ፣ ለሌላም እርሱ ብቻ ለሚያውቀው እኛ ግን ለማናውቀው ዓላማው ይጠቀምበታል። ክፉዎቹን ግን የክፋት ሥራቸዉ የሚገባውን ፍዳቸውን በፈታሒነቱ ይክፍላቸዋል።

አቤቱ አምላካችንና አባታችን እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህ ፈቃድህን እንድናውቅና እንድንፈጽም እርዳን፣ አሜን።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር